# “ ምጸተ ወያኔ - ሽብር ናፈቀኝ! ”

የጐንቻው !

እንደ ክረምት ሰማይ መብረቅ ያረገዘው የዝምታ ድባብ ደበረኝ፤
ሁካታ፤ ፍንዳታ፤ አኬልዳማ፤ ወያንኛ ሽብር ነሸጠኝ፤ ሽብር ናፈቀኝ፤
እንደ ጥቅምት ቁር አካሌን ሰቅዞ ከቆፈነኝ፤ መንፈሴን ከደበተኝ፤
ፈርቶ ከሚያስፈራ ኮሽታ ከተሳነው በድን ሕይወት ቢገላግለኝ፤
**እኔስ ሽብር አማረኝ፤አገሬውን ‘እግር-ተወርች’ ጠፍሮ እሚያፍታታኝ።**

የኰቴዬን ዳና ተከትሎ አቧራው ቢጤስ መንጋው ቢናኝ፤
የጐሸው እንዲደፈረስ፤በተቀበረው ደማሚት መገነጠ-ጢሱ እኒድያጥነኝ፤
ዛሬስ ውቃቤዬ አሻፈረኝ! እኔስ ምሴን አሰኘኝ፤ ሽብር፤ሽብር፤ሽብር አለኝ፤
**ድም!፤ ድም!፤ ድም! የሚል ፍንዳታ ሽብር፤ ግርግር ናፈቀኝ።**

መጥፊያዬም መዳኛዬ፤ ‘እንቆቅ’ ማርከሻዬ ሽብር ራበኝ፤ ሽብር ጠማኝ፤
እንደ በልግ ጎመን፤ እንደ ጸደይ እሸት፤ እንደ መኸር እህል አስቀናኝ፤
ዞትር በጎረቤት ሲበራይ፤ በኛ አውድማ ዙሪያውን ክምር አስፈራኝ፤
በኛ ጎጆ፤ በኛ ምድጃ ሃያ ዓመት ዓመድ ተጭኖ ያዳፈነኝ፤
**የግብራችን፤ ናፈቀኝ፤ በማሳችን በእሳት እንኩቶ እሚያበላ እሸት ውልብኝ።**

ሱማሌ እንኳ ‘ታድላ’ በአልሻባብ ባሩድ ታጥና ወኔ አጢሳ፤
አቃጥላ፤ ተቀጣጥላ የአገር ባላ፤ ምሰሶዋን ቆስቁሳ፤
ዓለም የሞቃት በዜና መረብ ተጦልባ ተገለባብጣ ተጠባብሳ፤
ተቋደስናት መቋድሾን የሽብር ሲሳያችን የአበሳሰልናትን ዓሳ፤
አስጋበዘችን የወዳጅነት ፌልሚያ ደግሳ፤
ልንክሳት፤ በሬሳ፤ ሙተን ስንድን ስማችን ገኖ እንዲነሳ፤
እንዲጎርፍልን ከወዳጃችን አሜሪካ ልገሳና ሙገሳ፤
‘እናመርታለን’ ‘ወዶ ዘማች’ እሚናፍቀው የሰው አገር አበሳ፤
**እሚሰዋ ሱዳን፤ ኢራቅ፤ አፍጋኒስታን ልማታዊ ፍኖ ለህይዎቱ የማይሳሳ።**

እኔስ ሽብር ናፈቀኝ ወያንኛ ‘ገድል ታሪኬን’ የሚያስወሳ፤
ድልድይ ሰባሪ፤ ቦምብ ቀባሪ፤ እሳት ጫሪ፤ ጉድጓድ ቆፋሪ፤ ደንደሳ፤
ፍንዳታ፤ ሁካታ፤ ሽብር አማረኝ፤ በአገር ሰደድ እሚያስነሳ፤
አንተ ማነህ? ባለ ሳምንት ተቃዋሚ፤ ግንቦት ሰባት ተወቀሳ፤
ፋታ ስጠኝ፤ በግርግር ማቄን፤ ጨርቄን እስካነሳ፤
**እኔስ ሽብር ሸተተኝ፤ ወያንኛ ፤ ቁም ተጠይቅ! ባለ አበሳ ተጠበሳ።**